# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

Commercial Bank of Ethiopia

ጋዜጣዊ መግለጫ 2020/21

## የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2020/21 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸምን አስመልክቶ የተዘጋጀ አጭር መግለጫ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከ140 ቢሊዮን ብር በላይ የተቀማጭ ገንዘብ መጠን በማሰባሰብ በታሪኩ ከፍተኛ የተባለውን ውጤት አስመዝግቧል፡፡

ባንኩ በበጀት ዓመቱ ከ20.3 ቢሊዮን ብር በላይ ዓመታዊ ያልተጣራ ትርፍ በማስመዝገብም ከፍተኛ የሚባል አፈፃፀም ያስመዘገበበት ዓመት ሆኖ ተጠናቋል፡፡

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሀገራችን የባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ የመሪነት ሚናውን እንዳስጠበቀ ላለፉት 80 አመታት መጓዝ የቻለ ባንክ ነው፡፡ የሀገሪቱን የልማት ፕሮጀክቶችና አጠቃላይ የልማት እንቅስቃሴ በፋይናንስ በመደገፍ፣ የባንክ አገልግሎት በመላ ሀገሪቱ በማስፋፋትና አዳዲስ በቴክኖሎጂ የተደገፉ የባንክ አገልግሎቶችን በማስተዋወቅ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

የሀገሪቱን ፈጣን ልማት ተከትሎ በመንግስትና በግሉ ኢንቨስትመንት የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ በመምጣቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይህንኑ የሚመጥን ምላሽ በመስጠት ላይ ነው፡፡

በተለይ እ.ኤ.አ በ2025 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የንግድ ባንክ ለመሆን ያስቀመጠውን ራዕይ ደረጃ በደረጃ በማሳካት ላይ ይገኛል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመትም ከዚህ ቀደም ከሚያደርገው ድጋፍ በተጨማሪ የህብረተሰቡን ማህበራዊ ችግሮች ለማቃለል የሚያግዙ ፕሮጀክቶችን በገንዘብና በቁሳቁስ በመደገፍ ተቋማዊ የማህበራዊ ኃላፊነቶቹን በከፍተኛ ደረጃ እየተወጣ ይገኛል፡፡

**በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ2020/21 በጀት አመት የስራ አፈጻጸም ስኬታማ የሚባል ሆኖ አልፏል፡፡**

**2. የተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2020/21 አጠቃላይ ተቀማጭ ገንዘብ ክምችትም እ.ኤ.አ ጁን 30 ቀን 2020 ከነበረበት 595 ቢሊዮን ብር ወደ 735 ቢሊዮን ብር ማድረስ ችሏል፡፡ አጠቃላይ የግል ተቀማጭ ገንዘብ (Private deposit) ክምችት 542.2 ቢሊዮን ብር ማድረስ ተችሏል፡፡ ይህን እውን ለማድረግም የህብረተሰቡን የቁጠባ ባህል ለማበረታታትና ለማሳደግ የሚረዱ የተለያዩ እቅዶች በማውጣት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ የተሻለ አፈፃፀም የተመዘገበባቸው የቁጠባ አይነቶችም የሴቶች፣የወጣቶች፣የታዳጊ ወጣቶች፣የሙዳይና የትምህርት የቁጠባ ናቸው፡፡

የሲ.ቢ.ኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት የሸሪዓ የፋይናንስ መርሆዎችንና አሠራሮችን የሚከተል፣ በአገልግሎት ወቅት ምንም ዓይነት ወለድ መክፈልም ሆነ መቀበል ላይ ያልተመሰረተና በሸሪዓ በተፈቀዱ ሥራዎች ላይ ብቻ በመሳተፍ እየተሰጠ የሚገኝ የባንክ አገልግሎት ነው፡፡

በዚህም ወለድን በመፍራት ምክንያት መደበኛውን የባንክ አገልግሎት መጠቀም ያልቻሉ ዜጎች የሲ.ቢ.ኢ ኑር አገልግሎትን እንዲጠቀሙ እያደረገ ይገኛል፡፡

- እ.ኤ.አ. በሰኔ 2021 መጨረሻ የሲ.ቢ.ኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ጠቅላላ የተቀማጭ ገንዘብ መጠን 52 ቢሊዮን ብር ማድረስ መቻሉ፣
- የሲ.ቢ.ኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎትን የሚጠቀሙ ደንበኞች ብዛትን 4.2 ሚሊዮን ማድረሱ፤

- በዚህ ዘርፍ በተለያዩ የስራ መስኮች ለተሰማሩ ደንበኞች የተሰጠ የፋይናንስ መጠን ብር 6.2 ቢሊዮን ብር ማቅረብ መቻሉ፣
- በመላ ሀገሪቱ አገልግሎቱን የሚሰጡ ቅርንጫፎች ብዛት 1700 ያደረሰ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ሙሉ በሙሉ የሲቢኢ ኑር ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ብቻ የሚሰጡት ቅርንጫፎች ቁጥር ደግሞ 75 ማድረስ ችሏል።

### 3. የውጭ ምንዛሬ ግኝት

የሀገሪቱን የልማት ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ እንዲቻል እንደተቀማጭ ገንዘብ ማሰባሰብ ሁሉ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ለማሳደግ በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። ባንኩ በበጀት አመቱ ከሀዋላ፣ ከውጭ ምንዛሬ እንዲሁም ከወጪ ንግድ ከ 2 ነጥብ 86 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ማሰባሰብ ችሏል። በዚህም ለተለያዩ ለግልና ለመንግስት የልማት ፕሮጀክቶች፣ አስፈላጊ የግብዓት አቅርቦት እንዲውል አድርጓል።

### 4. የብድር ስርጭትና አሰባሰብ ክንውን

ባሳለፍነው በጀት አመት ለልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችና ንግድ ተቋማት የሚውል 107 ቢሊዮን ብር በብድርና ቦንድ መልክ አዲስ ብድር ለደንበኞች ቀርቧል። በተጨማሪም በበጀት አመቱ 60 ቢሊዮን ብር ከብድር ተመላሽ ለመሰብሰብ ተችሏል።

### 5. ጠቅላላ ሀብት እና ትርፍ አፈጻጸም

በ2020/21 በጀት ዓመት መጨረሻ የባንኩ ጠቅላላ ሀብት ብር 999 ቢሊዮን ማድረስ የተቻለ ሲሆን፣ ዓመታዊ ትርፉም ከታክስና ከሌሎች ተቀናሾች በፊት ብር 20.3 ቢሊዮን ሆኗል። ይህ ትርፍ ሊገኝ የቻለው በዓለም አቀፍ ደረጃና በኢትዮጵያም የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ በኢኮኖሚው ላይ እያደረሰ ያለውን ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖና በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰቱ አለመረጋጋቶች የሚያደርሱትን ጫና በመቋቋም የተመዘገበ ነው። ባንካችን ያስመዘገበው ይህ ትርፍ በ80 ዓመት ጉዞው እጅግ ከፍተኛው ሆኖ የተመዘገበ ነው።

## 6. የባንክ አገልግሎት ተደራሽነት እና የኤሌክትሮኒክ ባንኪንግ አፈጻጸም

የባንክ አገልግሎትን ተደራሽ ከማድረግ አንፃር የባንክ ቅርንጫፎች በአሁኑ ጊዜ ከ1,700 በላይ ማድረስ ተችሏል፡፡ ሀገራዊ ቁጠባን ለማበረታታት የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎ ለተግባራዊነት በሚደረገው እንቅስቃሴ የአስቀማጭ ደንበኞች ቁጥር 31.4 ሚሊዮን ደርሷል፡፡ ከተደራሽነት ጎን ለጎንም የአገልግሎት ጥራትን በየጊዜው በማሻሻል ተመራጭ ባንክ ለመሆን የሚደረጉ ጥረቶች ውጤታማ እየሆኑ መጥቷል፡፡

ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባትም ህብረተሰባችንን ተጠቃሚ እያደረግን እንገኛለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባንካችን ከ6.7 ሚሊዮን በላይ የኤቲኤም ካርድ ተጠቃሚዎች ያሉት ሲሆን፣ በመላ ሀገሪቱም ከ3,091 በላይ የኤቲኤም ማሽኖችን እና ከ4,350 በላይ ፖስ መክፈያዎችን በልዩ ልዩ ቦታዎች በማስቀመጥ የክፍያ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ እያገዘ ይገኛል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከ5.2 ሚሊዮን በላይ የሞባይል የባንክ አገልግሎት፣ ከ31,000 በላይ የኢንተርኔት ባንክ አገልግሎት ተጠቃሚዎችም የአገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በዚህ ዓመት በሁሉም የዲጅታል ባንክ አገልግሎት ዘርፎች አገልገሎቶቹን ለማግኘት የተመዘገቡት ደንበኞች ቁጥር ከአምናው ተመሳሳይ ጊዜ ጋር ሲወዳደር በእጅጉ የላቀ ሲሆን ተመዝጋቢዎችን ሙሉ በሙሉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ግን ሰፊ የግንዛቤ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ ይታመናል፡፡ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዲጂታል ባንኪን አማካኝነት የሚከናወነው የገንዘብ ዝውውርም ከ56 በመቶ በላይ ሆኗል፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሲቢኢ ብር የባንክ አገልግሎት ደንበኞች ወደ ቅርንጫፍ መሄድ ሳይጠበቅባቸው አገልግሎቶችን በቀላሉና በፍጥነት ማግኘት የሚችሉባቸውን ከ16,500 በላይ ህጋዊ ወኪሎችን አፍርቷል፣የሲቢኢ ብር ነጋዴዎችም ከ24,900 በላይ ደርሰዋል፡፡ በዚህም ከ5ነጥብ 6 ሚሊዮን በላይ ደንበኞችን ተጠቃሚ ለማድረግ ተችሏል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የደንበኞቻችንን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ለመጨመርና ግብይቶች ከሂሳብ ወደ ሂሳብ እንዲከናወኑ በማገዝ cashless ማህበረሰብ የመፍጠርን ግቡን እውን ለማድረግ በየደረጃው ብርቱ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የባንካችንን የዲጂታል ባንክ አገልግሎት የሚጠቀሙ ደንበኞች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ ሲሆን ባሳለፍነው በጀት ዓመት ብቻ በዲጂታል ባንኪንግ አማካኝነት ከ529 ቢሊዮን ብር በላይ ዝውውር ተፈፅሟል፡፡ ለዚህ ውጤት መምጣት ደግሞ በበጀት ዓመቱ ማሻሻያ የተደረገበት የኮር ባንኪንግ ቴክኖሎጂ ከፍተኛውን ድርሻ አበርክቷል፡፡ በቀጣይም ይህን የኮር ባንኪንግ ስርዓት በመጠቀም የዲጅታል ባንክ አገልግሎት በስፋት ለመስጠት እንዲያስችል ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል፡፡

## 7. ማጠቃለያ

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባንኩን የ2025 ራዕይ ከማሳካት አንጻር እንዲሁም የሀገራችንን የፋይናንስ ዘርፍ ለማሳደግና የክፍያ ሥርአቱን ለማዘመን የሚረዱ የተለያዩ እቅድና ፕሮጀክቶችን በመንደፍ በበጀት አመቱ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን የተገኘውም ውጤት አበረታች ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ውስጥም ባንካችን ገና ወረርሽኙ ከመስፋፋቱ አስቀድሞ የመከላከል ስራዎችን የሰራንበት ዓመት ነው፡፡ ሰራተኞቻችንም በተናጠል በሚኖሩበት አካባቢ ለችግር የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን በገንዘብና በቁሳቁስ እየደገፉ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለገበታ ለሀገር ፕሮጀክት የ1ነጥብ1 ቢሊዮን ብር ድጋፍ ያደረግንበት ዓመት ሆኖ ተጠናቋል፡፡የገበታ ለሀገር ያደረገው የገንዘብ ድጋፍም ሶስት ቦታዎች ከአማራ ክልል ጎርጎራ፣ ከኦሮሚያ ክልል ወንጪ እና ከደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ኮይሻን በማልማት ቱሪዝምን ለማስፋፋት ለተነደፈው "ገበታ ለሀገር" ፕሮጀክትንለማልማት የሚያግዝ ሲሆን የእነዚህ ፕሮጀክቶቹ በግንባታ ሂደት ላይም ሆነ ተጠናቀው ለአገልግሎት ሲበቁ ለበርካቶች የስራ እድል ከመፍጠራቸውም በተጨማሪ የሀገርን ገፅታ የሚቀይሩና እና የቱሪስት መስህብ የሚሆኑ ማሳያ ፕሮጀክቶች ይሆናሉ፡፡